የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፲፪
አዲስ አበባ-የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

12th Year No. 12
ADDIS ABABA- 27th February, 2006

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፬፻፹፩/፲፱፻፺፰ ዓ.ም

የዕፅዋት አዳቃዮች መብት አዋጅ…ገጽ ፫ሺ፫፻፴፱

<u>CONTENTS</u>

Proclamation No. 481/2006

Plant Breeders' Right Proclamation …. Page 3339

## አዋጅ ቁጥር ፬፻ ፹፩ /፲፱፻፺፰

## ስለዕፅዋት አዳቃዮች መብት የወጣ <u>አ ዋ ጅ</u>

በምርምር የተገኙ አዳዲስ የዕፅዋት ዝርያዎችን መጠቀም የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ጉልህ አስተዋጽኦ የሚያበረክት በመሆኑ፣

አዳዲስ የዕፅዋት ዝርያዎችን በምርምር አዳቅሎ ማውጣት ከፍተኛ ጥረትና መዋዕለ ንዋይ የሚጠይቅ በመሆኑ፣

አዳዲስ የዕፅዋት ዝርያዎችን በምርምር አዳቅሎ በማውጣት ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች በመስኩ የሚያደርጉትን ጥረትና ኢንቨስትመንት ለማበረታታት ለሥራቸው ውጤት እውቅና መስጠትና የኢኮኖሚ ጥቅም እንዲያገኙበት ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የዕፅዋት አዳቃዮችን መብት ከማበረታታት ጐን ለጐን አዳዲስ የዕፅዋት ዝርያን በማውጣት ግብዓት የሆነውን የዕፅዋት ጀነቲክ ሀብት ጠብቀው ያቆዩትና ወደፊትም የሚጠብቁት የአገራችን አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ዘርን የመጠቀምና መለዋወጥ ለዘመናት የቆየው ልማዳዊ ሥርዓታቸው እንዲቀጥል ማድረግ አስፈላጊና ተገቢ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION NO. 481/2006.

### A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR PLANT BREEDERS' RIGHT

**WHEREAS**, the utilization of new plant varieties developed through research play a significant role in improving agricultural production and productivity;

**WHEREAS,** the development of new plant varieties requires considerable effort and investment;

**WHEREAS,** it is necessary to provide for recognition and economic reward for those who contribute to such effort and investment so as to encourage their involvement in the sector

**WHEREAS,** it is necessary and appropriate to ensure that the farming and pastoral communities of Ethiopia, who have been conserving and continue to do so in the future the agro-biodiversity resource used to develop new plant varieties, continue to their centuries old customary practice of use and exchange of seed;

**NOW,THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) of the Constitution, of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ ∩"የዕፅዋት አዳቃዮች መብት አዋጅ ቁጥር ፬፻፹፩/፲፱፻፺፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩/ "አመልካች"∪ ማለት የዕፅዋት አዳቃዮች መብት እንዲሰጠው ለሚኒስቴሩ ማመልከቻ ያቀረበ ሰው ነው፤

፪/ "ሚኒስቴር"∪ ማለት የግብርናና የገጠር ልማት ሚኒስቴር ነው፤

፫/ ∩"አዳቃይ"∪ ማለት፤

ሀ/ አዲስ የዕፅዋት ዝርያ አዳቅሎ ያወጣ ሰው፣ ወይም

ለ/ አዲስ የዕፅዋት ዝርያ አዳቅሎ ያወጣን ሰው ቀጥሮ ወይም ሥራውን ተኮ ናትሮ ያሠራ ሰው፣ ወይም

ሐ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ "ሀ " ወይም "ለ" የተጠቀሰው ሰው ወራሽ የሆነ ሰው ነው፣

፬/ ∩"ባለመብት"∪ ማለት የዕፅዋት አዳቃዮች መብት ከሚኒስቴሩ የተሰጠው ሰው ነው፣

፭/ ∩"አዲስ የዕፅዋት ዝርያ"∪ ማለት ቀጥሎ የተጠቀሱት ባህሪያት ያሉት የዕፅዋት ዝርያ ማለት ነው፣

ሀ/ በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ባህሪያት ምክንያት የዕፅዋት አዳቃዮች መብት ለማግኘት ማመልከቻ በቀረበበት ዕለት መኖራቸው በሕዝብ ከታወቁት ከሁሉም ሌሎች ዝርያዎች በግልጽ የሚለይ፣

ለ/ ከተደጋጋሚ ማራባትና ማባዛት በኋላም በእያንዳንዱ ዑደት መጨረሻ ልዩ መገለጫዎቹን ይዞ በመገኘት ዋና ዋና ባሕሪያቱን ሳይለውጥ የሚቆይ፣

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the " Plant Breeders' Right Proclamation No. 481/2006."

**2. Definitions**

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:-

1/ "applicant" means a person who has filed an application with the Ministry for a plant breeders' right ;

2/ "Ministry" means the Ministry of Agriculture and Rural Development;

3/ "breeder" mans a person who:

a) has bred and developed a new plant variety; or

b) has employed or commissioned the work of the person who has bred or developed a new plant variety; or

c) is a successor in title of the person mentioned in (a) or (b) of this Sub-Article;

4/ "holder" means a person to whom a plant breeders' right has been granted by the Ministry;

5/ "new plant variety" means a variety that:

a) by reason of one or more identifiable characteristics, is clearly distinguishable from all other varieties the existence of which is a matter of common knowledge at the date of application for a plant breeders' right;

b) is stable in its essential characteristics, in that after repeated reproduction or multiplication, at the end of each cycle, remains true to its description;

ሐ/ በዘር ወይም ያለ ዘር የሚራባበትን የተለዩ ባሕርያት በሚመለከት በበቂ ሁኔታ ወጥ የሆነ አንድ ዓይነት ዝርያ ወይም በደንብ ተለይቶ የሚገልጽ ሕብረ-ዝርያ የሆነ፣ እና

መ/ የዝርያው የዘር ቁስ ሌሎች ሰዎች ለንግድ አገልግሎት እንዲጠቀሙበት አዳቃዩ፣

፩/ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ከሆነ የዕፅ ዋት፣ አዳቃዮች መብት እንዲሰጥ ለሚ ኒስቴሩ ማመልከቻ ከቀረበበት ዕለት አንድ ዓመት በፊት፣ ወይም

፪/ በሌላ ሀገር ግዛት ውስጥ ከሆነና የዛፍ፣ የፍራፍሬ ዛፍ ወይም የወይን ዛፍ ዝርያዎችን በሚመለከት ሲሆን ማመል ከቻው ከቀረበበት ዕለት ከስድስት ዓመት በፊት ወይም ሌሎች ዝርያዎችን የሚመለከት ሲሆን ከአራት ዓመት በፊት ያልሸጠው ወይም በሌላ መንገድ አስተላልፎ ያልሰጠው ዝርያ ነው::

፮/ "ዕፅዋት" ማለት እንስሳ ያልሆነ እና በተፈጥሮ መራባት የሚችል ሕይወታዊ ሃብት ነው፣

፯/ "የተጠበቀ ዝርያ" ማለት ሚኒስቴሩ የዕፅዋት አዳቃዮች መብት ለአዳቃዩ የሰጠበት አዲስ የዕፅዋት ዝርያ ነው፣

፰/ "ዝርያ" ማለት በአንድ የዕፅዋት ቤተሰብ ውስጥ የታወቀ የመጨረሻ ዝቅተኛ ደረጃ ያለው የዕፅዋት ስብስብ ሆኖ፣

ሀ/ ከአንድ ከተወሰነ ጄኖታይፕ ወይም ከብዙ ጄኖታይፖች ጥምረት በሚመ ነጩ ባህሪያት መታየት የሚገልጽ፣

ለ/ ካሉት ባህሪያት ቢያንስ በአንዱ ከማና ቸውም ሌሎች የዕፅዋት ስብስቦች የሚለይ፣ እና

ሐ/ ባሕሪያቱን ሳይቀይር መራባት በመ ቻሉ ምክንያት እንደ አንድ ዓይነት ሊወሰድ የሚችል ነው፣

፱/ "የገበሬዎች ዝርያ" ማለት የራሱ የተለየ ባህሪ ያለውና የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች ያገኙት፣ ያዳቀሉት፣ ያጐለበቱት ወይም ያቆዩት ዝርያ ወይም የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች የሚያውቁት ዱር በቀል ዝርያ ማለት ነው::

c) having regard to its particular features of sexual reproduction or vegetative propagation, is sufficiently homogenous or is a well-defined multi-line; and

d) its material has not been sold or otherwise disposed of to others by the breeder for purposes of commercial exploitation of the variety:

i) in the territory of Ethiopia, earlier than one year before the date of filling of application for plant breeders' right with the Ministry; or

ii) in the territory of any other state, earlier than six years in the case of varieties of tree, fruit tree or grape vines, or in the case of other species, earlier than four years before the date of the application.

6/ "Plant" means a living organism which is not an animal and which can reproduce itself naturally.

7/ "protected variety" means a new plant variety that is protected by a plant breeders' right granted by the Ministry;

8/ "variety" means a plant grouping within a single botanical tax on of the lowest known rank, which can be :

a) defined by the expression of the characteristics resulting from a given genotype or combination of genotypes;

b) distinguished from any other plant grouping by the expression of at least one of said characteristics; and

c) considered as a unit for being propagated unchanged;

9/ "Farmers variety" means a plant variety having specific attributes and which has been discovered, breed, developed or natured by Ethiopian farming communities or a wild relative of variety about which the Ethiopian farming communities have common knowledge;

፲/ “ዱር በቀል ዝርያ” ማለት ለማዳ ያልሆነና በተፈጥሮ በዱር የሚገኝ የዕፅዋት ዝርያ ነው፣

፲፩/ “የዘር አካል” ማለት መራባት የሚችል ማንኛውም የዕፅዋት ክፍል ነው፣

፲፪/ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም ሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ው፣

፲፫/ “ድርጅት” ማለት በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው የመንግሥት ወይም የግል ድርጅት ነው፣

፫. <u>የአዋጁ የተፈጻሚነት ወሰን</u>

፩/ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ የሚሆነው ሚኒስቴሩ በመመሪያ በሚወስናቸው የዕፅዋት ቤተሰቦ ችና ዓይነቶች አዲስ የዕፅዋት ዝርያዎች ላይ ይሆናል፡፡

፪/ አዋጁ ተፈጻሚ የሚሆንባቸውን የዕፅዋት ቤተሰ ቦችና ዓይነቶች ዝርዝር ሚኒስቴሩ እንደአስ ፈላጊነቱ በየጊዜው ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>የዕፅዋት አዳቃዮች መብት</u>

፬. <u>የመብት መጠበቅ</u>

በዚህ አዋጅ የተደነገጉት ቅድመ ሁኔታዎችና የተጣሉ ገደቦች እንደተጠበቁ ሆኖ አዲስ የዕፅዋት ዝርያን ያወጣ አዳቃይ የዕፅዋት አዳቃይ መብት ይሰጠዋል፡፡

፭. <u>የዕፅዋት አዳቃዮች መብት ወሰን</u>

፩/ ከክልከላ ነጻ ስለመሆንና ስለገደቦች በዚህ አዋጅ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆኖ፣ የዕፀዋት አዳቃዮች መብት ባለቤት፣

ሀ) ሌሎች ሰዎች እንዲሸጡ ፈቃድ መስ ጠትን ጨምሮ የተጠበቀ ዝርያን ተክል ወይም የዘር አካል የመሸጥ፣ እና

ለ) ሌሎች ሰዎች እንዲያባዙ ፈቃድ መስጠትን ጨምሮ የተጠበቀ ዝርያን የዘር አካል ለሽያጭ የማባዛት፣ ብቸኛ መብት ይኖረዋል፡፡

10/ “Wild relative” means a plant variety which is not domesticated by man and which is found in the wild by nature.

11/ “Propagating material”means a plant variety which is not domesticated by man and which is found in the wild by nature.

12/ “Person” means natural person or juridical person.

13/ “Institution” means a state or private organization having juridical personality.

**3. Scope of Application**

1/ This Proclamation shall apply to new plant varieties of the genera and species, which the Ministry shall determine by directives;

2/ The Ministry may revise, from time to time, as necessary, the list of the plant genera and species to which this Proclamation shall apply.

## <u>PART TWO</u>
## <u>PLANT BREEDERS; RIGHT</u>

**4. Protection fo Right**

Subject to the conditions and limitations provided for in this Proclamation, a breeder shall be granted a plant breeders; right in respect of his new plant variety.

**5. Scope of Plant Breeder’s Right**

1/ Subject to the exemptions and restrictions provided for in this Proclamation, a plant breeders’ right entitles the holder an exclusive right to:

a/ sell, including the right to license other persons to sell, plants or propagating material of the protected variety; and

b/ produce, including the right to license other persons to produce, propagating material of the protected variety for sale.

፪/ የባለመብቱን ፈቃድ ያገኙ ካልሆነ በስተ ቀር የተጠበቀ ዝርያን በተመለከተ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሱትን ተግባራት ማከናወን ለሌሎች ሰዎች የተከለከለ ነው።

፮. <u>ከክልከላ ነጻ ስለመሆን</u>

፩/ የዕፅዋት አዳቃዮች መብት የተሰጠበት ቢሆንም ማናቸውም ግለሰብ ወይም የአርሶ አደሮች ማህበረሰብ የተጠበቀ ዝርያን በተመለከተ የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን አይከለከልም፤

ሀ) ለንግድ ላልሆኑ ሌሎች አገልግሎቶች የተጠበቀ ዝርያን ማራባት መዝራት ወይም መጠቀም፤

ለ) ለምግብነት ወይም የዝርያውን ማብ ቀል ወይም ማራባት ለሚያስከትሉ ሌሎች አገልግሎቶች እንዲውል የተ ጠበቀ ዝርያን ተክል ወይም የዘር አካልን መሸጥ፤

ሐ) የተጠበቀውን ዝርያ ተክሎች ወይም የዘር አካላት ተዘርተው በሚገኙበት ማሳ ላይ ወይም ተተክለው በሚገኙ በት ማናቸውም ሌላ ቦታ ላይ እንዳሉ መሸጥ፤

መ) ሌላ ዝርያን ለንግድ አገልግሎት ለማ ባዛት በተደጋጋሚ ከመጠቀም በስተ ቀር አዲስ የዕፀዋት ዝርያን ለማው ጣት የተጠበቀ ዝርያን ዘር ወይም የዘር አካል በመነሻ የተለያይነት ምንጭነት መጠቀም፤

ሠ) በምግብነት በቤት ውስጥ ለመጠቀም ወይም በምግብነት ለገበያ ለማቅረብ የተ ጠበቀ ዝርያን መዝራት፤

ረ) የተጠበቀ ዝርያን ለቀጣይ ማዳቀል፣ ለምርምር ወይም ለትምህርት አገልግ ሎት መጠቀም፤

ሰ) ጥቅም ላይ ስለሚውሉበት ሁኔታ የተቀ መጡ ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ከጅን ባንክ ወይም ከዕፀዋት ጀነቲክ ሀብት ማዕከላት የተጠበቀ ዝርያን ማግኘት።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ገበሬዎች ያመረቱትን የተጠበቀ ዝርያን ዘር ወይም የዘር አካል የተመሰከረለት ዘር አድርገው ለመሸጥ አይችሉም።

2/ The carrying out of the activities referred to in Sub-Article (1) of this Article by other persons with respect to a protected variety is prohibited unless with the authorization of the holder.

**6. Exemptions to Plant Breeders' Right**

1/ Notwithstanding the existence of a plant breeder's right, any person or farmers' community may:

a) propagate, grow and use a protected variety for purposes other than commerce;

b) sell plants or the propagating material of the protected variety for use as food or for any other use that does not involve growing the plant or the propagating material of the protected variety;

c) sell plants or propagating material of a protected variety as they are within a farm or any other place where plants of the variety are gown;

d) use plants or propagating material of a protected variety as an initial source of variation for purpose of developing another new plant variety except where the person makes repeated use of plants or propagating material of the variety for the commercial production of another variety;

e) sprout a protected variety for use as food for home consumption or for the market;

f) use a protected variety in further breeding, research or teaching;

g) obtain, with the conditions of utilization, protected variety from gene banks or plant genetic resources centers.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, farmers cannot sell farm-saved seed or propagating material of a protected variety in the seed industry on commercial scale.

## ፯. በዕፀዋት አዳቃዮች መብት ላይ የሚጣሉ ገደቦች

፩/ በሚከተሉት ምክንያቶች የተነሳ ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ሚኒስቴሩ በዕፅዋት አዳቃዮች መብት አጠቃቀም ላይ ገደብ ለማድረግ ይችላል፤

ሀ) በዕፅዋት አዳቃዮች መብት ባለቤቶች መካከል በሚደረግ ውድድር ምክንያት ችግር የተፈጠረ እንደሆነ፤

ለ) በምግብ ዋስትና፣ በሥነ-ምግብ ወይም የጤና ፍላጐቶች ወይም በብዝሀ ሕይወት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያደረሰ ሆኖ ከተገኘ፤

ሐ) ለገበያ የሚቀርበው የተጠበቀ ዝርያ ዘር አብዛኛው ከውጪ ሀገር የሚመጣ የሆነ እንደሆነ፤

መ) የአርሶ አደሩ ማህበረሰብ ለአንድ ለተወሰነ የተጠበቀ ዝርያ ዘር ያለው ፍላጐት ያልተሟላ የሆነ እንደሆነ፤

ሠ) በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶ ችና ሀገር በቀልና ሌሎች ቴክኖሎ ጂዎች እንዲያድጉ በማበረታታት የሕዝብን ጥቅም ማራመድ ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ በዕፀዋት አዳቃዮች መብት አጠቃቀም ላይ ገደብ ለማድረግ ሲወስን፤

ሀ) የተጣሉ ገደቦችን ዝርዝር በመግለጽ የውሳኔውን ግልባጭ ለባለመብቱ ይሰጣል፤

ለ) ገደብ ስለመጣሉ ለህዝብ ያሳውቃል፤

ሐ) ገደብ በመጣሉ ለባለመብቱ የሚከፈለ ውን ካሳ ይወስናል፡፡

፫/ ለባለመብቱ እንዲከፈል በተወሰነው ካሳ ላይ ባለመብቱ ቅር ከተሰኘ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፬ መሠረት ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡

## ፰. የግዴታ ፈቃድ

፩/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፰ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሚኒስቴሩ የሕዝብን ጥቅም ለመጠበቅና ፍላጐቱ ያለው ማናቸውም ሰው ሲያመለክት የግዴታ ፈቃድ ለመስጠት ይችላል፡፡

## 7. Restrictions on Plant Breeders' Right

1/ The Ministry may, when public interest so requires, due to the following grounds, put restrictions on the exercise of a plant breeders' right where:

a) problems arise due to competitive practices of holders;

b) food security, nutritional or health needs or biological diversity are adversely affected;

c) a high proportion of a protected variety offered for sale is being imported;

d) the requirements of the farming community for prorogating material of a particular protected variety are not met;

e) it is considered important to promote public interest for socio-economic reasons and for developing indigenous and other technologies

2/ When the Ministry decides to put restrictions on the exercise of a plant breeders' right, it shall:

a) give to the holder the copy of the decision setting out the particulars of the restrictions;

b) give public notice of the restrictions; and

c) specify the compensation to be paid to the holder.

3/ where the holder is dissatisfied with the compensation decided to be paid, he may lodge his appeal in accordance with Article 34 of this Proclamation.

## 8. Compulsory Licensing

1/ Without prejudice to the provisions of Article 8 of this Proclamation, the Ministry may, to safeguard public interest, grant a compulsory license upon application by any interested person

፪/ ሚኒስቴሩ የግዴታ ፈቃድ ሊሰጥ የሚችለው፣

ሀ) ባለመብቱ የተጠበቀውን ዝርያ ዘር ለጠቅላላው ሕዝብ ፍላጎት በሚበቃ መጠን የማያመርትና ለሽያጭ የማያቀርብ ከሆነና ሌሎች ሰዎች የተጠበቀ ዝርያውን ዘር እንዲያመርቱና እንዲሸጡ ፈቃድ የከለከለ ወይም ሚዛናዊ በሆነ የስምምነት ሁኔታ ሌሎች ሰዎች የተጠበቀ ዝርያውን ዘር እንዲያመርቱና እንዲሸጡ ፈቃድ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ፣ ወይም

ለ) የተጠበቀ ዝርያው ጥቅም ላይ እንዲውል ባለመብቱ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል ተብሎ ሊታሰብ የሚችልበት አንድም ሁኔታ የሌለ፣

እንደሆነ ብቻ ነው፡

፫/ ሚኒስቴሩ የግዴታ ፈቃድ በሚሰጥበት ጊዜ የግዴታ ፈቃዱ የተሰጠው ሰው ለባለመብቱ ሊሰጥ የሚገባውን ክፍያ፣ የግዴታ ፈቃዱ የሚቆይበትን ጊዜና እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ሁኔታዎችን ይወስናል፡፡ የግዴታ ፈቃድ የሚሰጥበት ጊዜ ከሦስት ዓመት ያነሰና ከአምስት ዓመት የበለጠ መሆን አይችልም፤ ሆኖም የግዴታ ፈቃዱ ጊዜ እንዲራዘም ጥያቄ ከቀረበና የግዴታ ፈቃድ ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑት ምክንያቶች ያልተወገዱ ከሆነ ሚኒስቴሩ ጊዜውን ለማራዘም ይችላል፡፡

፬/ የግዴታ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የባለመ ብቱ ፈቃድ ያስፈልጋቸው የነበሩ ተግባ ሮችን ሁሉንም ወይም አንዱን ለማከናወን ብቸኛ ያልሆነ መብት ይኖረዋል፡፡

፭/ የግዴታ ፈቃድ የተሰጠ መሆኑ ባለመብቱ ዝርያውን ከመጠቀም ወይም ሌሎች ሰዎች እንዲጠቀሙበት ፈቃድ ከመስጠት አያግደውም፡፡

**፱. <u>የዕፀዋት አዳቃዮች መብት ዘመን</u>**

የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የዕፀዋት አዳቃዮች መብት የሚቆይበት ዘመን ተቀባይትን ያገኘው የዕፀዋት አዳቃዮች መብት ማመልከቻ ገቢ ከሆነበት ዕለት አንስቶ ዓመታዊ ሰብሎችን በተመለከተ ለሃያ ዓመት፣ ዛፎችን፣ የወይን ተክሎችን ወይም ሌሎች ቋሚ ተክሎችን በተመለከተ ለሀያ አምስት ዓመት ይሆናል፡፡

2/ The Ministry may grant a compulsory license only if:

a) the holder is not producing and selling the propagating material of the protected variety in sufficient amount to meet the needs of the general public and has refused to license other persons to produce and sell the propagating material of the protected variety or is not willing to give such license under reasonable terms; or

b) there exist no condition under which the holder can be expected to give a permit to use his protected variety.

3/ Where the Ministry grants compulsory license, it shall determine the remuneration the person to whom the compulsory license is granted shall pay to the holder, the duration of the compulsory license and other conditions as necessary. The duration of a compulsory license shall not be shorter than three years and longer than five years; provided, however, that the Ministry may extend the duration if an application for extension is made and the conditions warranting compulsory licensing continue to exist.

4/ A person to whom a compulsory license is granted shall have a non-exclusive right to perform all or any of the activities for which the authorization of the holder would have been required.

5/ Compulsory licensing shall not preclude the holder from using the variety or to grant license to others.

**9. Duration of Plant Breeders Right**

Without prejudice to other provisions of this Proclamation, a plant breeders' right shall exist for a period of 20 years in the case of annual crops, and 25 year in the case of trees, vines and other perennial trees from the date the successful application for a plant breeders' right was accepted.

## ፲. የዕፅዋት አዳቃዮች መብት የሚሰጣቸው ሰዎች

፩/ አንድ አዳቃይ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ ሀገር ዜጋ ቢሆንም ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር ቢሆንም ባይሆንም እንዲ ሁም ዝርያው ኢትዮጵያ ውስጥ ወይም ውጭ ሀገር የተዳቀለ ቢሆንም አዲስ የዕፀዋት ዝርያውን በሚመለከት የዕፅዋት አዳቃዮች መብት ይሰጠዋል፡፡

፪/ ዝርያውን በጋራ በማደቀላቸው ወይም የጋራ ወራሾች በመሆናቸው ምክንያት ሁለት ወይም ከሁለት የበለጡ ሰዎች የዕፅዋት አዳቃዮች መብት ለማግኘት መብት ያላቸው በሆነ ጊዜ መብቱ ለሁሉ በጋራ ይሰጣቸዋል፤ ሆኖም ቀሪዎቹ በጽሑፍ ፈቃዳቸውን የሰጡ እንደሆነ አንዱ ብቻውን ወይም ከመካከላቸው የተወ ሰኑት ብቻቸውን የዕፅዋት አዳቃዮች መብት እንዲሰጣቸው ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡

፫/ አዳቃዩ የመንግሥት ወይም የግል ድር ጅት በሆነ ጊዜ የዕፅዋት አዳቃዮች መብቱ በድርጅቱ ስም ይሰጣል፡፡

፬/ አንድን የዕፅዋት ዝርያ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች ለብቻቸው በተናጠል ያዳቀሉ በሆነ ጊዜ የዕፅዋት አዳቃዮች መብት የሚሰጠው የዕፅዋት አዳቃዮች መብት እንዲሰጠው በመጀመ ሪያ ማመልከቻ ለሚኒስቴሩ ላቀረበው ሰው ይሆናል፡፡

፭/ የዕፅዋት አዳቃዮች መብት ለማግኘት መብት ያልነበረው ሰው ማመልከቻ አቅ ርቦ በተገኘ ጊዜ የዕፅዋት አዳቃዮች መብት ለማግኘት መብት ያለው ወገን ማመልከቻው ለእሱ እንዲዛወርለት ለሚኒስቴሩ ማመልከት ይችላል፡፡

## ፲፩. ማመልከቻ ስለማቅረብ

የዕፀዋት አዳቃዮች መብት እንዲሰጠው የሚፈ ልግ አዳቃይ ማመልከቻውን ለሚኒስቴሩ በጽ ሑፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ማመልከቻ የሚቀ ርብበት፣ የሚመረመርበትና ውሣኔ የሚሰ ጥበት ሁኔታና ሥርዓት በደንብ ይወሰናል፡፡

## ፲፪. ጊዜያዊ የመብት ጥበቃ

፩/ የዕፅዋት አዳቃዮች መብት ማመልከቻ ከቀረበበት ዕለት አንስቶ የዕፅዋት አዳቃ ዮች መብት እስከተሰጠበት ወይም ማመ ልከቻው ውድቅ እስከተደረገበት ዕለት ድረስ ባለው ጊዜ አዲስ የዕፅዋት ዝርያ ውን በተመለከተ አመልካቹ የዕፅዋት አዳ ቃዮች መብት እንዳለው ሆኖ ይቆጠራል፡፡

## 10. Persons Entitled to Plant Breeders Right

1/ A breeder shall be entitled to a plant breeders' right in respect of his new plant variety, whether or not the breeder is an Ethiopian national or a foreigner, or is an Ethiopian resident or not, and whether the variety was bred locally or abroad.

2/ Where two or more persons bred the variety jointly or that they are joint successors, they shall hointly be entitled to plant breeders' right; provided however, that only one or some of such persons may apply for a plant breeders' right provided that the remaining other persons have given their consent in writing to this effect.

3/ Where the breeder is a public or a private institution, the plant breeders' right shall be granted in the name of the institution.

4/ Where a variety has been bred by two or more persons independently of each other, the entitlement to plant breeders' right shall belong to the person who has first filed an application with the Ministry for plant breeders' right.

5/ Where an application is filed by a person who is not entitled to plant breeders' right, the person who is entitled to the plant breeders' right may apply to the Ministry for the assignment of the application to him.

## 11. Application

A breeder who wants to be granted a plant breeders' right in respect of new plant variety shall, present written application to the Ministry. The conditions and procedure in accordance with which applications may be lodged, examined and decided shall be specified by regulations.

## 12. Provisional Protection

1/ The applicant shall be deemed to have a plant breeders' right in respect of the new variety during the period between the date the application for plant breeders' right is filed and the granting of plant breeders'

፪/ በጊዜያዊ የመብት ጥበቃ ሥር የሚገኝ አዲስ የዕፀዋት ዝርያን የጀነቲክ ቁስ ከምርምር ውጪ ለሌሎች አገልግሎቶች መጠቀም አይቻልም። በጊዜያዊ የመብት ጥበቃ ሥር የሚገኝ አዲስ የዕፀዋት ዝርያን የጀነቲክ ቁስ ከምርምር ውጪ ለሌሎች አገልግሎቶች እንዳይውል ለማድረግ ሚኒስቴሩ አስፈላጊ የሆኑትን እርምጃዎች ይወሰዳል።

**፲፫. ማመልከቻን ስለመቃወም**

የዕፀዋት አዳቃዮች መብት ለማግኘት ማመል ከቻ በቀረበ ጊዜ ለአመልካቹ የዕፀዋት አዳቃ ዮች መብት ቢሰጥ በሕዝብ ጥቅም ላይ ጉዳት ይደርሳል ወይም ዝርያው የዕፀዋት አዳቃዮች መብት ለመስጠት የሚያስፈልጉትን መስፈር ቶች አያሟላም ወይም አመልካቹ ለማመል ከት መብት የለውም ብሎ የሚያምን ማናቸ ውም ሰው መቃወሚያውን ለሚኒስቴሩ ለማቅ ረብ ይችላል። መቃወሚያ የሚቀርብበትና ውሣኔ የሚሰጥበት ሁኔታና ሥርዓት በደንብ ይወሰናል።

**፲፬. የዕፀዋት አዳቃዮች መብት ስለመስጠት**

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸ ውን ሲያረጋግጥ የዕፀዋት አዳቃዮች መብት ይሰጣል፤

፩/ የዕፀዋት ዝርያው አዲስ የሆነ እንደሆነ፤

፪/ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የዕፀዋት አዳቃዮች መብት ለአመልካቹ እንዳይሰጥ የሚያስከለክል ምክንያት የሌለ እንደሆነ፤

፫/ ዝርያውን አዳቅሎ ለማውጣት ጥቅም ላይ የዋለውን የጀነቲክ ሀብት አመልካቹ በተገቢው የአርክቦት ሕግ መሠረት ያገኘ መሆኑ ያረጋገጠ እንደሆነ፤

፬/ በአዲስ የዕፀዋት ዝርያ ላይ የዕፀዋት አዳቃዮች መብት ቀደም ሲል ለሌላ ሰው ያልተሰጠ እንደሆነ፤

፭/ ዝርያውን በተመለከተ ቀደም ሲል የቀረበና ያልተነሳ ወይም ውድቅ ያልተደረገ የዕፀዋት አዳቃዮች መብት ማመልከቻ የሌለ እንደሆነ፤ እና

፮/ የዕፀዋት አዳቃዮች መብት ለመስጠት መከፈል ያለበት ክፍያ ሁሉ የተከፈለ እንደሆነ።

**፲፭. የዕፀዋት አዳቃዮች መብት መዝገብ**

ሚኒስቴሩ የዕፀዋት አዳቃዮች መብት መዝገብ

right or the final rejection of the application

2/ The genetic material of the new plant variety under provisional protection shall not be used for non-research purposes. The Ministry shall take the necessary measures to prevent the use of the genetic material of such variety for non-research purposes.

**13. Opposition**

Where an application is lodged for a plant breeders' right, any person, who considers that the granting of plant breeders' right will be contrary to public interest, or that the variety does not fulfill the requirements for granting plant breeders' right, or that the applicant is not entitled to plant breeders' right, may lodge with the Ministry an opposition to the application setting out the particulars for the opposition. The conditions and procedure pursuant to which opposition shall be lodged, examined and disposed shall be specified by regulations.

**14. Granting of Plant Breeders' Right**

The Ministry shall grant a plant breeders' right if it is satisfied that:

1/ the plant variety is new;

2/ there is no ground, as provided for in this Proclamation, to refuse the granting of plant breeders' right to the applicant;

3/ the breeder has a proof that he has obtained the genetic resource used to develop the variety in accordance with the relevant laws on access to genetic resources;

4/ a plant breeders' right has not been granted to another person in respect of the variety;

5/ there has been no earlier application, that has not been withdrawn or rejuected, for a plant breeders' right in respect of the new variety in question; and

6/ all fees payable in relation to the granting of plant breeders' right have been paid.

**15. Register of Plant Breeders' Right**

ይይዛል:: በዕፅዋት አዳቃዮች መብት መዝገብ ዝርዝር ጉዳዮች በደንብ ይወሰናሉ::

**፲፮. <u>የዕፀዋት አዳቃዮች መብትን ለሕዝብ ስለማሳወቅ</u>**

ሚኒስቴሩ የዕፅዋት አዳቃዮች መብት ሲሰጥ የዕፅዋት አዳቃዮች መብት የተሰጠ መሆኑን ለሕዝበ ያሳውቃል::

**፲፯. <u>ናሙና ማስቀመጥ</u>**

የዕፅዋት አዳቃዮች መብት የተሰጠበትን ዝርያ ማንበር እንዲቻል ሚኒስቴሩ የዝርያውን ናሙና ባለመብቱ ለብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት እንዲሰጥ ማድረግ አለበት::

**፲፰. <u>ዝርያውን ስለማደስ</u>**

፩/ የዕፅዋት አዳቃዮች መብት በተሰጠበት ዕለት ያሉትን ባህርያት የዕፀዋት አዳቃዮች መብት ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ሁሉ ዝርያውን ይዞ እንዲቆይ ለማድረግ ባለመብቱ ዝርያውን የማደስ ግዴታ አለበት::

፪/ ሚኒስቴሩ ዝርያው የታደሰ መሆኑን ለማረጋገጥ ባለመብቱ የዝርያውን ዘር ወይም ሌላ መረጃ እንዲያቀርብ ለመጠየቅ ይችላል::

**ክፍል ሦስት**
**<u>የዕፀዋት አዳቃዮች መብትን ስለማስተላለፍና ስለመሠረዝ</u>**

**፲፱. <u>የመብት መተላለፍ</u>**

፩/ የዕፀዋት አዳቃዮች መብት በውል ወይም በሕግ ለሌሎች ሰዎች ሊተላለፍ ይችላል::

፪/ የዕፀዋት አዳቃዮች መብትን በውል ለማስተላለፍ ውሉ በዕፅዋት አዳቃዮች መብት መዝገብ ካልተመዘገበ በስተቀር ውጤት አይኖረውም::

**፳. <u>የዕፅዋት አዳቃዮች መብትን ስለመተው</u>**

፩/ ለሚኒስቴሩ በማሳወቅ የዕፅዋት አዳቃዮች መብትን ለመተው ይቻላል::

፪/ ሚኒስቴሩ መብትን የመተው ማስታወ ቂያ ሲደርሰው ባለመብቱ መብቱን የተወ መሆኑን በዕፅዋት አዳቃዮች መብት መዝ ገብ ያስገባል፤ ሕዝብም ያሳውቃል::

The Ministry shall keep a register of plant breeders' rights. The particulars that may be entered in the register shall be specified by regulations.

**16. Publication of Plant Breeders' Right**

Where the Ministry grants a plant breeders' right, it shall give public notice to that effect.

**17. Deposition of Samples**

The Ministry shall, for the purpose of conservation, cause that the holder deposits at the Institute of Biodiversity Conservation sample of the new plant varieties with respect to which a plant breeders' right have been granted.

**18. Maintenance of Variety**

1/ The holder shall have the obligation to maintain the variety to ensure that all the characteristics of the variety at the date of granting the right are maintained throughout the duration of the plant breeders' right.

2/ The Ministry may, to ensure that the variety is maintained, require the holder to furnish material of the variety or any other necessary information.

**<u>PART THREE</u>**
**<u>TRANSFER AND REVOCATION OF PLANT BREEDERS' RITHT</u>**

**19. Transfer of Right**

1/ Plant breeders' right may be transferred to other persons by a contract or by the law.

2/ A transfer of plant breeders' right by a contract may have no effect unless entered in the register of plant breeders' right.

**20. Surrender of Plant Breeders' Right**

1/ A holder may surrender his plant breeders' right by giving notice to the Ministry.

2/ Upon receiving notice of surrender, the Ministry shall enter same in the register of

ሮሺ.ፎ፻፺፱

፫/ የዕፀዋት አዳቃዮች መብትን በሚመለከት በፍርድ ቤት ክርክር በመካሄድ ላይ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ካልፈቀደ ወይም ተከራካ ሪዎቹ ወገኖች ካልተስማሙ በስተቀር ሚኒስቴሩ መብት የመተው ጥያቄውን አይቀበልም።

**፳፩. ለማይገባው ሰው ስለተሰጠ የዕፀዋት አዳቃዮች መብት**

፩/ የዕፀዋት አዳቃዮች መብት ለማይገባው ሰው የተሰጠ በሆነ ጊዜ መብቱን ማግኘት ይገባው የነበረው ሰው የተሰጠው የዕፀዋት አዳቃዮች መብት ለእሱ እንዲዛወርለት ለሚኒስቴሩ ማመልከት ይችላል።

፪/ መብት እንዲዛወር የቀረበውን ማመል ከቻና የባለመብቱን ምላሽ ከመረመረ በኋላ ሚኒስቴሩ መብቱ ለማይገባው ሰው መስጠቱንና ለአመልካቹ መሰጠት የሚገባው መሆኑን ካረጋገጠ መብቱ በዚሁ መሠረት እንዲዛወር ያደርጋል።

**፳፪. የዕፅዋት አዳቃዮች መብትን ስለመሠረዝ**

፩/ ከሚከተሉት ምክንያቶች አንድ ሲያጋጥም ሚኒስቴሩ የዕፅዋት አዳቃዮች መብትን መሠረዝ አለበት፤

ሀ/ ዝርያው አዲስ አለመሆኑ ከተረጋገጠ ወይም መብት ከመሰጠቱ በፊት ቢታወቅ ኖሮ መብቱ እንዳይጥ ሊያስደርግ የሚችል መረጃ የተገኘ እንደሆነ፣

ለ/ ባለመብቱ የዕፀዋት አዳቃዮች መብ ትን በሚመለከት መክፈል ያለበትን ክፍያ የመክፈል ጊዜው የደረሰ ለመሆኑ ማስታወቂያ ከተሰጠው ዕለት አንስቶ በዘጠና ቀናት ውስጥ ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ፣ ወይም

ሐ/ ባለመብቱ ዝርያውን ሳያድስ የቀረ እንደሆነ።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩ መሠረት ሚኒስቴሩ የዕፀዋት አዳቃዮች መብትን ለመሠረዝ ውሳኔ ላይ ከደረሰ ለመሠረዝ የበቃበትን ምክንያት በመግለጽ ለባለመ ብቱ የጽሑፍ ማስታወቂያ መስጠትና መብቱ የተሠረዘ መሆኑን ለሕዝብ ማስታወቅ አለበት።

plant breeders right and give public notice thereof.

3/ Where an action in respect of a plant breeders' right is pending before a court, the Ministry shall not register the surrender except by leave of the court or by consent of the parties in the court proceeding.

**21. Plant Breeders' Right Granted to a Person not Entitled to**

1/ Where aplant breeders' right has been granted to a person who is not entitled to, the person who is entitled to the plant breeders' right may apply to the Ministry demanding that the plant breeders' right be transferred to him.

2/ The Ministry shall, upon examining the application for the transfer and the response of the holder and ascertaining that the right has wrongly been granted to the holder and that the applicant is entitled thereto, cause the plant breeders' right to be transferred accordingly.

**22. Revocation**

1/ The Ministry shall revoke a plant breeders' right if;

a) it is proved that the variety was not new or that facts exist which, if known before the granting of the right, would have resulted in the refusal of the right;

b) the holder has failed to pay the prescribed fee payable in respect of the plant breeders' right within 90 days after having been notified that the payment has fallen due; or

c) the holder has failed to maintain the variety.

2/ Where the Ministry decides to revoke a plant breeders' right in accordance with Sub-Articlee (1) of this Article, it shall give written notice of the revocation to the holder

**፳፫. <u>የዕፅዋት አዳቃዮች መብትን እንዲሠረዝ ስለማመልት</u>**

የዕፅዋት አዳቃዮች መብት በመሠጠቱ ጥቅሙ የተነካበት ማናቸውም ሰው ተሰጥቶ የነበረው የዕፅዋት አዳቃዮች መብት በዚህ አዋጅ መሠረት እንዲሰረዝ ለሚኒስቴሩ ማመልከት ይችላል፡፡ የዕፅዋት አዳቃዮች መብት እንዲ ሠረዝ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚመረመር በትና ውሣኔ የሚያገኝበት ሥርዓት በደንብ ይወሰናል፡፡

**ክፍል አራት**
**<u>ስለዕፅዋት አዳቃዮች መብት መጣስ</u>**

**፳፬. <u>መብት የመጣስ ድርጊት</u>**

የተጠበቀ ዝርያን በተመለከተ የባለመብቱን ፈቃድ ማግኘት የሚገባ ሆኖ ሳለ የባለመብቱ ፈቃድ ሳይገኝ የተፈጸመ ማናቸውም ድርጊት የዕፅዋት አዳቃዮች መብትን የመጣስ ድርጊት ይሆናል፡፡

**፳፭. <u>ዳኝነት ስለመጠየቅ</u>**

፩/ የዕፅዋት አዳቃዮች መብቱ የተጣሰበት ባለመብት መብቱን የመጣስ ድርጊቱ እንዲቆምና ለደረሰበት ጉዳት ካሳ እንዲከፈለው በፍርድ ቤት ክስ ለማቅረብ ይችላል፡፡

፪/ ተጣሰ የተባለው የዕፅዋት አዳቃዮች መብቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫/፩/ ድን ጋጌ መሠረት መሠረዝ ያለበት መሆኑን ተከሳሹ ካላስረዳ በስተቀር፣ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ መብቱን የመጣስ ድርጊቱን እንዲያቆምና በባለመብቱ ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሣ እንዲከፈል ይወሰንበታል፡፡

**፳፮. <u>የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ</u>**

፩/ የዕፅዋት አዳቃዮች መብትን በመጣስ ክስ የቀረበበት ተከሳሽ ተጣሰ የተባለው የዕፅዋት አዳቃዮች መብት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫/፩/ ድንጋጌ መሠረት ሊሠረዝ የሚገባው ከሆነ መብቱ እንዲሰረዝ በመ ጠየቅ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ለማቅረብ ይችላል፡፡

፪/ በቀረበው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫/፩/ ከተጠቀሱት ምክንያቶች አንዱ መኖሩ ከተረጋገጠ ፍርድ ቤቱ ክርክር የተነሳበት የዕፅዋት አዳቃዮች መብት

stating the grounds for the decision, and it shall give public notice of the revocation.

**23. Application for Revocation**

Any person whose interest is affected by the granting of a plant breeders' right may apply to the Ministry for the revocation of the plant breeders' right in accordance with this Proclamation. The procedure in accordance with which an application for revocation of plant breeders' right may be examined and decided shall be specified by regulations.

**<u>PART FOUR</u>**
**<u>INFRINGEMENT OF PLANT BREEDERS' RIGHT</u>**

**24. Act of Infringement**

Any act in respect of a protected variety for which the authorization of the holder is required and which is done without such authorization shall constitute an act of infringement of a plant breeders' right.

**25. Legal Action**

1/ A holder whose plant breeders' right has been infringed may institute an action in court to require the cassation of the act of infringement and claim compensation for damage.

2/ The court shall order the cessation of an act of infringement and the payment of compensation for the damage caused on the holder unless the defendant forthwith proves that the plant breeders' right alleged to have been infringed has to be revoked in accordance with the provisions of Article 23 (1) of this Proclamation.

**26. Counter Claim**

1/ A defendant in an action against infringement may institute a counter claim for the revocation of the plant breeders' right in question, if it is revocable in accordance with Article 23 (1) of this Proclamation.

2/ The court shall order the revocation of the

እንዲሠረዝ ያዛል፡፡



፫/ የዕፅዋት አዳቃዮች መብት እንዲሰረዝ ፍርድ ቤቱ ያዘዘ እንደሆነ ተከሳሹ የፍ ርድ ቤቱን ትዕዛዝ ግልባጭ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት፡፡ ሚኒስቴሩም የፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ሲደርሰው የዕፅዋት አዳ ቃዮች መብቱ የተሠረዘ መሆኑን በመዝ ገብ ያስገባል፣ መሠረዙንም ለሕዝብ ያስታውቃል፡፡

## ክፍል አምስት
## የገበሬዎች መብት

**፳፯. መሠረቱ**

የገበሬዎች መብት የሚመነጨው የአካባቢ አርሶ አደሮች ለምግብና ለግብርና መርት ለሚውል የማዳቀል ሥራ መሠረት የሆኑትን የዕፅዋት ጀነቲክ ሀብት በማንበርና በዘላቂነት በመጠቀም ካበረከቱትና ወደፊትም ሊያበረክቱ ከሚችሉት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ነው፡፡

**፳፰. የገበሬዎች መብት**

፩/ የዕፅዋት ዝርያዎችን በመጠቀም ረገድ ገበሬዎች የሚከተሉት መብቶች ይኖሯ ቸዋል፣

ሀ/ ካመረቱት የገበሬ ዝርያዎች ምርት ላይ ዘር ወይም የዘር አካል የማስቀ መጥ፣ የመጠቀም፣ የመለዋወጥና የመሸጥ መብት፣

ለ/ የተጠበቁ ዝርያዎችን ከጂን ባንክ ወይም ከዕፅዋት ጀነቲክ ሃብት ማዕ ከላት የሚገኙ ዝርያዎችን ጨምሮ፣ ገበሬዎች ዝርያዎችን ለማውጣት የመጠቀም መብት፣

ሐ/ የተጠበቀ ዝርያን ዘርተው ከሚያገ ኙት ምርት ዘርን በጋራ የማስቀ መጥ፣ የመጠቀም፣ ማባዛትና የማዘጋ ጀት መብት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገ ገው ቢኖርም፣ ገበሬዎች ከተጠበቀ ዝርያ ካመረቱት ምርት ላይ ያገኙትን ዘር ወይም የዘር አካል በዘር ኢንዱስትሪው ውስጥ ለንግድ በሆነ መጠን ለመሸጥ አይችሉም፡፡

plant breeders' right in question, if any of the grounds specified in Article 23(1) of this Proclamation is proved to exist by the counter claim.

3/ Where the court orders the revocation of the plant breeders' right, the defendant shall serve the copy of the court order to the Ministry. Upon receiving the court order, the Ministry shall register the revocation of the plant breeders' right and give public notice of the revocation.

## PART FIVE
## FARMERS' RIGHT

**27. Principle**

Farmers' Right stem from the enormous contributions that local farmers have made and will continue to make in the consersvation and sustainable use of plant gentitic resources that constitute the basis of breeding for food and agricultural production.

**28. Farmers' Right**

1/ In relation to the use of plant varities, farmers shall have the following rights:

a) to save, use, exchange and sell farm-saved seed or propagating material of farmers' varieties;

b) to use protected varieties indluding material obtained from gene banks or plant genetic resource centres to develop farmers' varieties;

c) to save, use, multiply, process and sell farm-saved seed of protected varieties.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, farmers mayy not sell farm-saved seed or propagating material of a protected variety in the seed industry as a certified seed.

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፳፱. ቅ ጣ ት**

የዕፅዋት አዳቃዮች መብትን የተላለፈ ማንኛውም ሰው መብቱን በመተላለፍ ያገኘውን ዘር ወይም የዘር አካል መወረሱ ሳይቀር ከስድስት ወር በማያንስ እሥራት እና ከብር አምስት ሺህ በማያንስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

**፴. ይግባይ ስለማቅረብ**

የዕፅዋት አዳቃዮች መብት መስጠትን፣ መከልከልን፣ መሠረዝን ወይም መገደብን በተመለከተ በሚሰጥ ውሳኔ ላይ ቅሬታ የተሰማው ወገን ውሳኔው በደረሰው በስልሣ ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል፡፡

**፴፩. ስለክፍያዎች**

የዕፅዋት አዳቃዮች መብትን በተመለከተ የሚደረጉ የክፍያዎች መጠንና አከፋፈል በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

**፴፪. ደንብ የማውጣት ሥልጣን**

ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፴፫.ተፈጻሚ ስለማይሆኑ ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

**፴፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## PART SIX
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**29. Penalty**

Any person who infringes a plant breeders' right shall, in addition to the confiscation of the seed or propagating material of the protected variety which is the proceed of the infringement, be punished with imprisonment not exceeding thereee years or a fine upto five thousand Birr or with both such imprisonment and fine.

**30. Appeals**

A party who is aggrieved of a decision on the granting, refusal, revocation or restriction of a plant breeders, right may lodge an appeal to the federal high court within sixty days from the date of receipt of the decision.

**31. Fees**

The amount and schedule of payment of fees to be paid in relation to plant breeders' right shall be determined by regulations to be issued hereunder.

**32. Issuance or Regulations**

The Council of Ministers may issue regulations for the proper implementation of this Proclamation.

**33. Implacable Laws**

No law, regulation, directive or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, have effect in respect of matters provided for by this Proclamation.

**34. Effective Date**

This Proclamation shall come in to force upon publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 27th day of February, 2006**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**